# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 246 ጥር 23 2005 ገጽ 1


አምባገነኖች መውደቂያቸው ሲደርስ ሁሉም ነገር በቁጥጥራቸው ሥር ያለ ለማስመሰል መቅበጥበጣቸው የተለመደ ነው። የወያኔም መቅበጥበጥ ምክንያቱ መሠረቱ እየተናደ በመሆኑ ነው። ቢቻለው የተፈጥሮ ቀመርን ሳይቀር በሱ መልካም ፈቃድ የሚከናወን መሆኑን ብናምለት ደስታው ነው። ይህ የሁሉም አምባነኖች የመውደቂያ ወቅት መለያ ባህርይ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መቀሌ ዉስጥ ህወሀት ለሁለት መሰንጠቁን የሚጠቁሙ ወረቀቶች መበተናቸዉ ተሰማ

ላለፉት ስድስት ወራት በተለይ ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ በአባላቱ የእርስ በርስ ሽኩቻና የቃላት ጦርነት ሲታመስ የከረመዉ የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ ግንባር ጭራሽ ለይቶለት ሁለት ቦታ የመሰንጠቅ አደጋ ላይ መዉደቁ የማይቀር መሆኑን የሚጠቁሙ በራሪ ወረቀቶች መቀሌ ዉስጥ በመበተን ላይ መሆናቸዉን ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ከመቀሌ በላኩልን ዜና ገለጹ። ባለፈዉ ረቡዕና ሀሙስ መቀሌ ዉስጥ ለህወሀት አባላትና ለከተማዉ ህዝብ በትግርኛ ቋንቋ ተጽፎ የተበተነዉ ወረቀት ስዩም መስፍንን፤ አባይ ፀሐዬንና ፀጋዬ በርሔን ከነባለቤቱ ከህወሀት እንዲባረሩ የሚጠይቅ ሲሆን ለህወሀት ክፍፍልና ያለመስማማት ዋና ምክንያት ነዉ ያላቸዉን የድርጅቱን መስራቾች ስብሐት ነጋንና አንዳንድ ጓደኞቹን ደግሞ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ይጠይቃል። በትናንትናዉ ዕለት ከወደ መቀሌ በደረሰን ዜና መሠረት ወረቀቱን የበተኑት እነ ቴዉድሮስ ሃጎስ፣አዜብ መስፍንና በረከት ስምኦን መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል።

የተበተነዉ ወረቀት "ሕዝባችን አስተውል" የሚል ሀይለ ቃል ያለበት ሲሆን ሆኖም ወረቀቱ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠዉ እነሱ ህዝብ የሚሉት የትግራይን ህዘብን ብቻ ነዉ። ወረቀቱን የበተነዉ ቡድን ለህዝብ ባስተላለፈዉ መልዕክት ዉስጥ «ተቆርቋሪ ለሆናችሁ የትግራይ ተወላጆች በሙሉ፤ «ድርጅታችሁ ህወሀት እስከ ዛሬ ታግላ እዚህ ደረጃ አድርሳችኋለች። በተለይም የሁሉም ነገር አድራጊና ፈጣሪ የነበረውን ባለ ራዕይ መሪያችንን በቅርብ ጊዜ አጥተናል። ዛሬ እነዚህን ደካማ ጐኖች ተጠቅመው ለጠላት አሳልፈው ሊሰጡን የሚፈልጉ ያውም ደግሞ ህዝብ የኔ የሚላቸው ጅቦች ተነስተውብናል የሚሉና የትግራይ ህዝብ ከተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በጠላትነት እንዲተያይ የሚገፍፉ ቃላቶች ተደርድረዉበታል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ ኢህአዴግ ለምርጫ ተብየው ቅስቀሳ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እየበተነ ሲሆን ባንጻሩ ሕዝቡ በምርጫ እንዳይሳተፍ ጥሪ መቅረቡ ታወቀ

ወያኔ ኢህአዴግ በመጪው ሚያዚያ ወር አካሂዳለሁ ላለው የአዲስ አበባ፣ የድሬዳዋ ከተሞች እና የክልል ምክር ቤቶች እና የወረዳዎች ምርጫ ተብየ ድራማ በርካታ ሰዎች የምርጫ ካርድ እንዲያወጡ ቤት ለቤት ቅስቀሳ እያካሄደ ሲሆን ለሚቀሰቅሱለት ካድሬዎቹ የቀን ውሎ አበል እና የስብሰባዎችና ድግሶች የሚያወጣው ገንዘብ አስደንጋጭ እየሆነ መምጣቱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ አመለከተ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ወያኔ ኢሃዴግ ቤት ለቤት እንዲቀሰቅሱ መልምሎ የላካቸው በርካታ ሰዎች በዝቅተኛ ገቢ ላይ የሚገኙ እናቶችን፣ ሴቶችን እና ወጣቶችን ከሴቶች ሊግ፣ ከወጣቶች ሊጎች እና ፎረምና ወጣት ማህበራት እና ዝቅተኛ የየአካባቢው ካድሬዎቹን ሲሆን በቀን ከሃምሳ ብር እስከ 250 እንደ ቀኑ ውጤታቸውና ደረጃቸው እየከፈለ መሆኑ ታውቋአል።

በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንን በድህነት አለንጋ መገረፍ እንደ መጠቀሚያ መሳሪያ እየተገለገለበት የሚገኘው ጨክላኝ አገዛዝ ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችን የአንበሳ አቡቶቡስ ቴኬት ቆራጭነት፣ በየሴክተርና የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በተላላኪነት፣ በአትክልተኝነት፣ በጥበቃ ሠራተኝነት ለመቅጠር ቃል በመግባትና የድጋፍ ደብዳቤ በመስጠት እንዲሁም ነቃ ያሉ ወጣቶችን ደግሞ ተደራጅተው በሚፈልጉት የሥራ መስክ እንዲሰማሩ የገንዘብ ብድርና የመሥሪያ ቦታ ለማመቻቸት ቃል እንደገባላቸው ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል። እንዲህም ሆኖ የወያኔው ኢሃዴህግ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በሙስሊም እስረኞች ላይ አሻንጉሊቱ የወያኔ ፍርድ ቤት ማንነታቸው የማይታወቁ ምስክሮችን ቃል እያስተናገደ ነው

በተለያዩ ሁኔታዎችና ወቅቶች ታፔላ እየተለጠፈባቸው የሚከሰሱና በሚታሰሩ እስረኞች ላይ ግፍና በደል በመፈጸም የሚታወቀው ዘረኛው የወያኔው አገዛዝ አሻንጉሊት ፍርድ ቤት ቅጥፈት የተሞላበትና የልጅ ጨዋታ የሆነ አስቂኝ የችሎት ውሎን እያስተናገደ ሲሆን፣ በዝግ ችሎት እየተካሄደ ባለው የሙስሊም መሪዎች የፍርድ ቤት ውሎ 190 ምስክሮች እንደሚቀርቡ ከገለፀ በሁአላ እስካሁን የቀረቡት ምስክሮች ቁጥር 11 ብቻ መሆኑ ታወቀ። የአዲስ አበባው የግንቦት ሰባት ራዲዮ ዘጋቢ ባስተላለፈልን በዚሁ ዘገባው በአሻንጉሊቱ ፍርድ ቤት እየታየ ያለው ክስ የመስማት ሂደቱ በ10 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል ቢባልም፣ በአሁኑ አካሄድ አቃቢ ህግ የምስክሮችን ቁጥር ካልቀነሰ በስተቀር በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥም ላይጠናቀቅ ይችላል ብሉአል።

ዘጋቢያችን የውስጥ ምንጮችን በመጥቀስ በላከልን ሪፖርት እንዳመለከተው የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ አቃቢ ህግ ምስክሮችን ሲያቀርብ ማንነታቸውን ሳያሳውቅና ለይስሙላ የአባታቸው ስም ነው የተባለን መጠሪያ ብቻ በመጠቀም መሆኑ ታውቁአል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተከሳሾቹ ጠበቃ የሆኑት አቶ ተማም አባቡልጋ እንደተናገሩት ምስክሮቹ የመኖሪያ አድራሻቸው ፣ ስራቸውና ማንነታቸው እንዲገለጥ ለዳኞቹ ቢያመለክቱም፣ ዳኞቹ "የምስክሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ምስክሮቹ አድራሻቸውንም ሆነ ስራቸውን እንዲገልጡ አይገደዱም" የሚል ምክንያት በመስጠት ጥያቄውን አለመቀበላቸው ታውቁአል። አቶ ተማም " በህገመንግስቱ አንቀጽ 20 መሰረት አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ሊታይ የሚገባው አገር ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል ሲሆን ብቻ ነው በማለት " ቢከራከሩም ዳኞቹ " የምስክሮች ደህንነትም አገር ደህንነት ነው" በሚል አሳፋሪ የምክንያት አሰጣጥ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጋቸውን ዘጋቢያችን በላከው ሪፖርት አመልክቱአል።

ዘጋቢያችን አክሎ እንደገለጸው ጠበቃ ተማም " በ1997 ዓም በቅንጅት መሪዎችና ጋዜጠኞች የፍርድ ቤት ሂደት ላይ እንደተደረገው የተከሳሾች ቤተሰቦች እና ዘመዶች ባይቀርቡ እንኳን ቢያንስ የውጭ እና የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና የውጭ ዲፕሎማቶች እንዲገኙ ችሎቱ ፈቃድ ይስጥ በማለት ቢጠይቁም" ዳኞቹ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው ክርክሩ ያለታዛቢ እንዲቀጥል መደረጉ ታውቁአልል።

በችሎት ተብየው ውሎ የተገኙ የአይን እማኞችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን እንደገለጸው ምስክሮቹ ተከሳሾች በአደባባይ የተናገሩትን ከመድገም ውጭ እስካሁን አንድም አዲስ ነገር አልተናገሩም። ምስክሮቹ የተመሰከረባቸውን ተከሳሾች ጠቁሙ ሲባሉ ሌሎችን ሰዎች እንደሚጠቁሙ፣ እስረኞችም በምስክሮች ድርጊትና በፍርድ ቤቱ ሂደቱ ድራማ እየተዝናኑ መሆኑ ታውቋል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአማራ ተወላጆች ላይ የሚያደርሰው የሰብአዊ መብት ረጋጣ ተባብሶ ቀጥሏል

በደቡብ ኢትዮጵያ ቤንች ማጂ ዞን ጉርዳፈርዳ እየተባለ በሚጠራው ቦታ በአማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰው የሰብአዊ መብት ረገጣ መቀጠሉን ኢሳት በትናንትናው እለት ምንጮቹን በመጥቀስ ባወጣው ዘገባ ላይ አመለከተ።

ኢሳት የመኢአድ ም/ሊ/መንበር የሆኑትን አቶ ወንድማገኝ ደነቀ በመጥቀስ እንደዘገበው በዚሁ ጉርዳፈርዳ እየተባለ በሚጠራው ቦታ አንዲት የ8 ልጆች እናት በጥይት የተገደሉ ሲሆን፣ ሁለት ህጻናት ደግሞ በመስተዳድሩ መኪና ተገጭተው መሞታቸውን ታውቁአል።

ታህሳስ 28/ 2005 ከምሽቱ 4 ሰአት ሲሆን 5 መሳሪያ የታጠቁ ወተዳሮች የ8 ልጆች እናት የሆኑትን ወ/ሮ አይቼሽ ስጦታውን በመኖሪያ ቤታቸው እንደገደሉዋቸው ዘገባው ያመለከተ ሲሆን ጥር 15 ቀን 2005 ዓ/ም ደግሞ የ4 እና የ7 አመት ህጻናት በመስተዳድሩ መኪና ተገጭተው ህይወታቸው ማለፉን ከአቶ ወንድማገኝ ማብራሪያ ለመረዳት መቻሉን ኢሳት ገልጹአል።

በብሄር ጥላቻ ላይ ተወልዶ፣ አድጎና ጎልምሶ በእርጅና ዘመኑ ኢትዮጵያዊያንን ግፍና መከራ እያበላ ያለው ይሄው ዘረኛ አገዛዝ ሌሎች 23 የአማራ ተወላጆችን በወህኒ ቤት አጉሮ በማሰቃየት ላይ መሆኑን የመኢአድ ተቀዳሚ የፐም/ል ፕሬዚዳንቱ ማከላቸውን ኢሳት ገልጹአል።

## ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ለመክፈል እኛም ዝግጁዎች ነን!

ቅኝ ገዥዎችን በማሳፈር በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ተጋድሎ ነጻነቷን ጠብቃ የኖረችውና በባርነት ስር ለቆዩ ሀገራት ፋና ወጊ የሆነችው ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ዛሬ በሀገር ውስጥ ወራሪ በሆነው ህወሃት/ወያኔ መዳፍ እጅ ገብታ በሁሉም ረገድ ከኢኮኖሚ እስከ ሰበአዊ መብት አያያዝ በአለም የመጨረሻዋ የሰው ልጅ መብት ረገጣ የሚፈጸምባት ተስፋ አልባ ሀገር ተብላ ተመድባ ትገኛለች።

ይህችው የቀድሞዋ ኢትዮጵያ በክብርና በኩራት የአፍሪካ የነጻነት ፋናወጊ ተብላ የሚነገርላት፤ በዚህ ዘመን በባርነት አረንቋ እየኖረች፣ ህዝቧ የነጻነት ያለህና የትውልድ የድረሱልኝ ጥሪ ኤሎሄ ለወጣት ልጆቿ እያቀረበች፣ እየተማጸነች አለች።

ይህን ተከትሎ በሁሉም ግንባር ሀገር በቀል ወራሪ ህወሃት/ወያኔን ታግሎ ለማስወገድ እየተደረገ ያለው ትብብር የሚበረታታ ቢሆንም የወያኔን የከፋፍለህ ግዛ ና የአንድ ዘር የበላይነት ርዕዮተ ዓለምን አስወግዶ ነፃነት ከናፈቀው ህዝብ ጎን በመሰለፍ በሀገራችን የሰላም አየር በሁሉም ከተሞች እንዲሰፍን ለሚደረገው እልህ አስጨራሽ ጉዞ የምናደርገው እገዛ በቂ ነው ብለን አናምንም።

ትውልዱ ለውጥ አያመጣም በሚል እስከአሁን የተደላደለውን ወያኔ፤ ከመንበሩ ፈንቅለው ሊጥሉት ዛሬ ራሳቸውን መሰዋእት ለማድረግ ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ፣ በታሪክ ማህደር ኢትዮጵያዊ ገድላቸው እንዲቀለምላቸው ቆርጠው የተነሱት የህዝባዊ ሃይል ታጋዮች ፤ የእማማ ኢትዮጵያን እንባ በእንባቸው ሊጠርጉ መከራና ስቃይን መርጠው መሰደዳቸውን ሰሞኑን በድጋሜ አስታውቀዋል።

ህዝባዊ ሃይሉ ከኢሳት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ "ኢትያጵያዊነት እንደ ሸቀጥ የተሸጠበት የክፉ ቀን ውረደት ላይ እንገኛለን እና ከገባንበት የውረደት አዘቅት የመውጫ ጊዜው አሁን ነው፤ ነገም ሳይሆን ዛሬ ነው። ዛሬ በሃገራችን በወያኔ አምባገነናዊ እብሪት ያልታፈነ፣ ያልተዋረደና ያልተዘረፈ የሃገሪቱ ዜጋ አይገኝም። የወያኔ ሹማምንት በሃብት ላይ ሃብት፤ በድሎት ላይ ድሎት ሲጨምሩ፤ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ እጣ ፈንታ ግን መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መንገላታት፣ መታሰር፣ መደብደብና መገደል ሆኗል" ብለዋል ። ታዲያ እኛ ምን እንጠብቃለን?

ሀገራችን ሀገር ሆና ለቀጣዩ ትውልድ ለማስረከብ ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ከማንኛውም ሃይል ጋር ሆኖ ለድረሱልኝ ሀገራዊ ወገናዊ ጥሪ ደራሽ በመሆን በዛች ሀገር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወያኔን በማስወገድ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታን ለማምጣት አምርሮ በመስራት ፍትህና ነፃነትን ከተጠማው ሕዝብ ጋር አብሮ ሊታገል ቃል በመግባት ለጥሪው ምላሽ ይሰጣል፡፡

የማንኛውም የፖለቲካ/የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም ወጣቱ፤ በተለይም አደገኛ በረሃዎችንና ባህሮችን በማቋረጥ ለመሰደድ ልብህ እየከጀለ ያለው የሃገራችን ወጣት ሆይ! የመተባበሪያው ጊዜ አሁን ነው። በውርደት እስከ መቼ ? ማንስ መጥቶ ሊታገልልን ይችላል? ስለዚህ በከንቱ ክቡር ህይወትን ከማጣት ስደትን አቁሞ ዘላለማዊ ክብር ወደ ሚያስገኝለት የትግል ጥሪ ይቀላቀል ዘንድ ግንቦት 7 ንቅናቄም ጥሪውን ያቀርባል።

በርግጥም ነው ድሎት ሳይሆን የህዝብ ስቃይ ጣርን፣ የሀገር ውርደትን ማየት አላስችል ያላቸው የህዝባዊ ሃይሉ የቁርጥ ቀን ወጣቶች፤ የጥቁር ደም ጥቁር አፈር የሰራቸው የአበው ልጆች የውርደትን ወላፈን፤ በማይቆምና በሚያቃጥል የትግል ወላፍን ሊመክቱት፣ ሊያስወግዱት፤ ተራራ፣ ጋራ ሸንተረሩን መርጠው ወያኔንን በሚገባው ቋንቋ ሊያናግሩት ሊጋፈጡት ቀናትን እየቆጠሩ ነው።

የህዝብ ልጆች የከፈሉትና ወደፊትም የሚከፍለው ውድ መስዋእትነት የሌላ አምባገነናዊና ግፈኛ ሥርዓት መቋቋሚያ እንዳይሆን ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ተግባር በተናጠል ይሁን በ ጋራ በመሆን መሰዋእት በመክፈል አብሮ መስራት የግድ ነው ሲል ግንቦት 7 ንቅናቄም ያምናል።

አምባገነኖች መውደቂያቸው ሲደርስ ሁሉም ነገር በቁጥጥራቸው ሥር ያለ ለማስመሰል መቅበጥበጣቸው የተለመደ ነው። የወያኔም መቅበጥበጥ ምክንያቱ መሠረቱ እየተናደ በመሆኑ ነው። ቢቻለው የተፈጥሮ ቀመርን ሳይቀር በሱ መልካም ፈቃድ የሚከናወን መሆኑን ብናምለት ደስታው ነው። ይህ የሁሉም አምባነኖች የመውደቂያ ወቅት መለያ ባህርይ ነው።

ስለዚህ ወያኔ ከሥልጣን ሳይባረር አንዳችም በጎ ለውጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ማሰብ አይቻልም። ስርአቱ ከገባበት የምቾት ማጥ ውስጥ በስብሶ ስለተቀመጠ ከቶ ጆሮዎቹ ለሰላማዊ ጥሪ ጮኸት የተደፈኑ ስለሆኑ፤ እያንዳንዷን ደቂቃ ሳንዘናጋ በንቃት ሁሉንም የተቃዋሚ ሃይላትን በማስተባበር ትግሉን የማቀጣጠያ ሰአት ላይ ነን።

እኛ ግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ከማንኛውም ሃይል ጋር ሆነን ለድረሱልኝ ሀገራዊ፣ ወገናዊ ጥሪ ደራሽ በመሆን፤ በዛች ሀገር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወያኔን በማስወገድ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታን ለማምጣት አምርሮ በመስራት ፍትህና ነፃነትን ከተጠማው ሕዝብ ጋር በመቆም ለመታገል ዝግጁ መሆኑን ዛሬም ያሳውቃል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## የከምሴ ሙስሊሞች የሀይማኖት መሪያችንን አናስወስድም በማለት ከወያኔ ጋር ተጋፈጡ

ኢሉባቡር ውስጥ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች ሼህ ሳሊህ አብዱልቃድር የተባሉትን የእስልምና ሀይማኖት መሪ በእብሪት ለመውሰድ በሄዱበት ወቅት ህዝቡ ግለሰቡን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከወያኔ ፖሊሶች ጋር ግጭት መፈጠሩን ዘጋቢያችን ከስፍራው የሚገኙ የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ በላከልን ዘገባ አመለከተ። ዘጋቢያችን እንደገለጸው ግጭቱ የተከሰተው ከምሴ በመባል በሚጠራውና ከመቱ ከተማ 15 ኪሜ ርቀት ላይ ሚገኝ ቦታ ነው።

ዘጋቢያችን በላከው ዘገባ እኚሁ ሼህ ሳሊህ አብዱልቃድር ከዚህ ቀደም በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በሽብርተኝነት ተከሰው 8 ወራት ከታሰሩ በሁዋላ መረጃ አልተገኘባቸውም በሚል በነጻ ተለቀው እንደ ነበር የታወቀ ሲሆን ባለፈው ሳምንት ፖሊሶች እንደገና ወደ አካባቢው በመሄድ የእርሳቸውን ጓደኛ ካሰሩ በሁአላ፣ በትናንትናው እለት ደግሞ ሼኩን ለማሰር ወደ ቀበሌው ሲሄዱ ህዝቡ በነቂስ በመውጣትና ተከቢራ በማለት በመቃወሙ በህዝቡና በፖሊስ መካከል ፍጥጫ ተከስቶ እንደ ነበር ታውቋአል። የህዝቡ ስሜት ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆነባቸው የዘረኛው አገዛዝ ፖሊሶች ሁሌም እንደሚያደርጉት በቀጥታ ወደ ግጭት ከማምራት ይልቅ ከህዝቡ ተወካዮች ጋር ለመነጋጋር መምረጣቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜና በተለይም የአገዛዙ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች የነበረው አለመረጋጋትና የህዝቡም የእምቢ ባይነት ስሜት እየጨመረ መምጣቱ በስፋት እየተዘገበ እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም የኢትዮፕያዊያን ተቃውሞ ሲጠነክርበት የሚሆነውን በማጣት የሚደነባበረው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የህዝብን ቁጣ ማቀዝቀዝና አቅጣጫ ማስቀየርን እንደዋነኛ አማራጭ እየተጠቀመበት ይገኛል።

ይህ በንዲህ እያለ ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ መጡበት አካባቢ የተመለሱ ከ700 የማያንሱ የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ፤ ጥያቄያቸው ካልተመለሰ ትምህርት ለመጀመር እንደሚቸገሩ እየገለጹ መሆኑን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ። ኢሳት ያነጋገራቸውን ተማሪዎች ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው በዩኒቨርስቲው በሙስሊም ተማሪዎች ላይ የሚደርሰው ጭቆና የሚጀምረው " ወደ ግቢ ለመግባት በሚደረገው ፍተሻ ነው" ካለ በሁዋላ በትናንትናው እለት ወደ አዲስ አበባ የተመለሱ ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ጋር በመሆን በትምህርት ሚኒስቴር በመገኘት ጥያቄያቸውን ለማቅረብ እቅድ ተይዞ እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል ብሉአል።

---

### መቀሌ ዉስጥ ህወሀት ለሁለት መሰንጠቁን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ ህዝብን ከህዝብ ጋር በሚለያይና ለጥፋት በሚዳርግ መልከ ተጽፎ የተበተነዉ ጽሁፍ "እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል መስራቾች ነን" ብሎ እራሱን ካወደሰ በኋላ ህወሀት ወደኋላ መገፍተሩን ብሎም በአንፃሩ ሌሎች ህወሀት ያሳደጋቸዉ ድርጅቶች መጠናከራቸዉንና ይህም የትግራይን ህዝብ ጥቅም እንደጎዳዉ ያለምንም ሀፍረት በመዘርዘር ከዚህ አደጋ ዉስጥ መውጣት ካለብን ከድርጅቱ የተወገዱትን የቀድሞ አባላት መልሰን ወደ ፓርቲው ማስገባት አለብን። ይህ ካልሆነ ግን የሕዝብ ትግል አውላላ ሜዳ ላይ ጅብ በልቶት ሊቀር ነው በማለት ከጠላቶቻችን ጋር እንታረቅ እያሉን ነውና "ሕዝባችን አስተውል" እያለ አንደኛዉን አንጃ ይከስሳል። ከላይ ከፍ ሲል አንደተጠቀሰዉ ክሱን የሚያቀርበዉ የአዜብ መስፍን፤ በረከት ስምኦነና ቴዎድሮስ ሀጎስ ቡድን ሲሆን ክሱ የሚቀርበዉ ደግሞ በነስዩም መስፍንና አባይ ጸሐዬ ቡድን ላይ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ጽሁፉ ስብሀት ነጋን የዚህ ሁሉ አፍራሽ ሴራ ጠንሳሽና አራማጅ ነዉ በማለት ይኮንነዋል።

ህወሀት ኢትዮጵያ ዉስጥ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋል የመከፋፈል አደጋ ሲገጥመዉ ይህ ሁለተኛ ግዜዉ ሲሆን የመጀመሪዉን አደጋ መለስ ዜናዊ ተቃዋሚዎቹን በማሰርና ከድርጅቱ በማባረር ማሰታገስ መቻሉ የሚታወስ ነዉ። አሁን ግን ህወሀት ይህ ነዉ ተብሎ የሚታይና የሚፈራ መሪ ስለሌለዉ ይህ መከፋፈልና መባላት ለ38 አመቱ ድርጅት የመጨረሻዉ መጀመሪያ ሊሆን ይችላል ሲሉ ብዙዎች አስተያየት በመስጠት ላይ ናቸዉ።

---

## በደል እንዴት ይራሳል? (ክፍል 2 የመጨረሻ )

ሰኞ ግንቦት 8 ቀን 1997 ዓም ረፋዱ ላይ የአዲስ አበባ አየር ሞገዶች ቅንጅት አዲስ አበባን አሸነፈ በሚል ድምጽ ተሞሉ። ተስፋ ቤቱ አልበቃ አለዉ፤ እሱም ሆነ ወላጆቹ ምኞታቸዉ የደረሰ መሰላቸዉና ያንን ከሆድ ዉስጥ ተፈንቅሎ የሚወጣ እዉነተኛ ደስታና ፈገግታ አይቶት የማያዉቀዉን ቤት ሥርግና ምላሽ አስመሰሉት።ተስፋ ኢትዮጵያ የምትመራዉ እናትና አባቱ በመረጡት ፓርቲ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አባቱ የነገሩት የእሱ የራሱ ብሩህ ዘመን መምጣት ወለል ብሎ ታየዉና የልጅነት ፊቱ በደስታ ተሞላ። ሆኖም አየሩን የሞላዉ ተቃዋሚዎች አዲስ አበባም አሸነፉ የሚል ዜና ነዉ እንጂ ምርጫዉን አሸነፉ የሚል ስላልነበረ እሱም፤ ወላጆቹም ሆኑ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሸንፈዉ ወያኔ ተወገደ የሚለዉን ዜና እስኪሰሙ ድረስ ልባቸዉ አላርፍ አለ።

ተስፋ ምድር ላይ ከኖረባቸዉ ጥቂት አመታት ይልቅ ሰኞ ግንቦት ስምንት ማክሰኞና ግንቦት ዘጠኝ ረቡዕ ግንቦት አስር እንደ ገመድ ረዘሙበት። በየደቂቃዉ ከአባቱ፤ ከእናቱና ከመንደሩ ሰዉ ሹክ እያለ ጆሮዉ ዉስጥ የሚገባዉ ዜና “ቅንጅት አሸነፈ” ሲል ፊቱ ላይ የተደቀነዉ ቴሌቪዥን ደግሞ ኢህአዴግ አሸነፈ ይላል። ቅንጅት አሸነፈ ሲባል ፊቱ በደስታ ይፈለቀለቃል፤ ኢህአዴግ አሸነፈ ሲባል ደግሞ ያንኑ ያክል ሰዉነቱ ይፈርሳል። ሁለቱም እንደማያሸኘፉ ያዉቃልና ትክክለኛዉን አሸናፊ አስከሚያዉቅ ድረስ አንቅልፍ አልወስድህ አለዉ።

ሀሙስ ግንቦት 11 ቀን ጧት ረፋዱ ላይ ተስፋ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቴሌቪዥኑን ዘጋዉና … አላልኩሽም . . . እማይ. . . . አላልኩሽም እያለ ከሳሎን ወጥቶ ወደ ኩሽና ገባ። እናቱ ልጃቸዉ ተስፋ ድምጽ ሰጥተዉ የመጡ ቀን የተናገራቸዉንም ሆነ አሁንም ሊነግራቸዉ የሚፈልገዉን ያዉቃሉና እሳቸዉም ልክ እንደ ልጃቸዉ በቅንጅት ያበበዉ ተስፋቸዉ በወያኔ ሲጠወልግ ታያቸዉ። ከሰዐታት በፊት ሙሉ አካላቸዉ በተስፋ ተሞልቶ የነበረዉ እናትና ልጅ የጫነዉን ጭንት ገልብጦ እንደሚመለስ ገልባጭ መኪና ባዶ ሆኑ። ተስፋ ጆሮዉን ከፍቶ ባዳመጠ ቁጥር “ድዉ ድዉ” የሚለዉ የራሱ ልብ ትርታ አስደነገጠዉና ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደከዳ እሱም ልቡ የሚከዳዉ መሰሎት ግራ ደረቱን በሁለት እጆቹ ይዞ ቆመ።

ግንቦት፤ ሰኔና ሐምሌ እያለ አመቱ እድሜዉ እየጨመረ ሲያረጅ የተስፋና የጓደኞቹ ከቅንጅት ማበብ ጋር አብቦ የነበረዉ ተስፋቸው ጨለመ። እነሱ ባያረጁም ተስፋቸዉና ያለሙት ህልም ዘመን እንደቆጠረ ሰዉ አረጀ። ተስፋ የቆረጡ ጋቢያቸዉን እየለበሱ እቤታቸዉ ተቀመጡ፤ የትግሉ ዉስብስበብነት የገባቸዉ ግን ወያኔን በሚችሉት ዘርፍ ሁሉ ለመታገል ታጥቀዉ ተነሱ። “የህዝብ ድምጽ ይከበር” የሚል ህዝባዊ ጥያቄና ጩኸት አዲስ አበባንና የክልል ከተሞችን አናወጠ። ህዝብና ወያኔ መርጠኸኛል. . . . የለም አልመርጥኩህም ብለዉ ሙግት ዉስጥ ገቡ። አዲስ አበባ ቀዉጢ ሆነች። ህዝብ ለመጮህ ድምጹን አግአዚ ልሳን ለመዝጋት መትረየሱን ተሸክሞ በየአደባባዩ ተፋጠጡ። የመለስ ዜናዊ “በሷቸዉ” የሚል የእብሪትና የበቀል ትዕዛዝ አዲስ አበባን አሸበራት፤ የአዲስ አበባ ሰማይ በሞት ዳመና ተሸፈነ። ከግራዚያኒና ከደርግ እልቂት አገግማ የሰነበተችዉ አዲስ አበባ እንደገና አገረሸባት። ስንት ልግደል እያለ እንዳበደ ዉሻ የሚክለፈለፈዉ አግአዚ በሬሳ ላይ እሬሳ ከመረ። እንደ ሞገስ አስገዶም፤ አብርሃም ደቦጭና እንደ ብዙዎቹ የ1970ዎቹ ሰማዕታት የህፃን ተስፋ ያኢድሜ ጓደኛ የነበረው ህጻን ነቢዩም ያልጠገበዉን ጨቅላ ህይወት ገብሮ አንቀላፋ። ተቃዊሚዎች አሸንፈዉ ዩኔንም የወደፊት የአገር መሪ የመሆን በር ይከፈታሉ ብሎ ሲጠባበቅ የነበረዉ የዚያን ጊዜው ህጻን ተስፋ በፋሺስቶች በግፍ የተጨፈጨፉትን ወገኖቹን በተለይም ምንም በማያውቀው የእድሜ ጓደኛው ህጻን ነቢዩ ኃይሌ አሰቃቂ አገዳደል ስሜቱ በመነካቱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድ ነጻነት ሲል ከአረመኔው የአግአዚ ሓይል ጋር ፊት ለፊት ለመተናነቅና ለመጋፈጥ ወሰነ።አዎ! በ1983 ዓም መለስ ዜናዊ ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ ግድያ አብቅቷል ብሎ ከተናገረ ከአመታት በኋላ የተወለደዉ ህፃን ነቢዩ ኃይሌ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ተገደለ።

ያቺ የቀን ጎዶሎ መጥታ ከሄደች ከሰባት አመት ከመንፈቅ በኋላ ዛሬም ልጆቿን በጠራራ ፀሐይ የተቀማችዉ አዲስ አበባ የፍትህ ያለህ እያለች ነዉ። ልጆቻቸዉ እንደወጡ የቀሩባቸዉ ወላጆች ፊት ዛሬም በእምባ እንደታጠበ ነዉ። ተስፋዉ እንደ መብረቅ ብልጭ ብሎ ድርግም ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብም የአግአዚ ጭካኔ ወዲህ ቢለዉ ወድያ ትርጉም አልሰጥህ ብሎት ዛሬም በሀዘን እንደተዋጠ ነዉ። እኛንና ዉድ አገራቸዉን ብለዉ ደረታቸዉ በአግአዚ አልሞ ተኳሾች የተበሳዉ ነቢዩና ጓደኞቹም ከላይ ከሰማይ “በደል ይረሳል…..በደል የለመዳል” ብለዉ መጠየቅ ከጀመሩ እነሆ ሰባት አመታት አለፉ። ወገን ለመሆኑ በደል ይረሳል ወይስ ይለመዳል? ህፃኑ ሰማእት ነቢዩ ኃይሌ በደል ስንለምድና በደል ስንረሳ እያየ ምን ይለን ይሆን . . . . እሱማ በመንፈስ እንዲህ ይለናል::

በደል እንዴት ይረሳል እንዴት ይለመዳል በደል
የኔ የነቢዩ የህጻኑ ደረት በአግአዚ ብረት ሰተረተር፤
ወንድ ሴት ሳይለይ ህዝብ በታንክ ሲገፈተር።

እኮ ንገሩኝ በደል እንዴት ይለመዳል
እናቶች በአረር ሽታ ሲታጠኑ
መንገዶች በወገን ደም ሲታጠቡ።

እባካችሁ አታስጨሁኝ መልሱልኝ ጥያቄዬን
አትብሉት አደራዬን።

በደል እንዴት ይረሳል ልጅ እናቱ ፊት ተረሽኖ
ነብስ ያላወቀ ህፃን እንደ ዲያቢሎስ ተኮንኖ።

በሉኮ ንገሩኝ አናግሩኝ ወይ ላናግራችሁ በተዘጋዉ አንደበቴ
ጎንበስ ብዬ ልማጸናችሁ በህጻንነት በተቀማዉ ህይወቴ።

እዉነት በደል ይረሳል? በይኮ ንገሪኝ ኢትዮጵያ በደል ይለመዳል?
በደል እንዴት ይለመዳል ከጎናችን ሰዉ ሲገደል፤
በደል እንዴት ይረሳል አበሻ ስጋዉ አንደ ነዶ ሲነደል።

አረ ንገሩኝ በደል እንዴት ይረሳል ሴት ልጅ ታስራ ጅማቷ ሲወጠር ፤
ወንድ የፊጥኝ ታስሮ ዉስጥ እግሩ ሰተለተል።

ስማኝ ወገኔ በደል እንዴት ይረሳል እታለም ታስራ ጡቷ ሲቆነጠጥ
ወንድም ጋሻ ታስሮ ብልቱ ሲጎተት።

በልኮ ንገረኝ አንተ ያገሬ ልጅ በደል እንዴት ይለመዳል፤
እህትህ ቁልቁል ስትሰቀል ወንድምህ ወፌ‌ይላላ ተሰቅሎ ሲቀቀል፤
እኮ ንገረኝ በደል እንዴት ይረሳል ህዝብ በጅምላ ሲነቀል፤
ወያኔ ወገንህን በዉሸት ቂምበቀል ሲበቀል።

ለመድኩት አልሽኝ እታለም እናቴ ፊት መገደሌን
አንተስ ወንድምዬ ረሳሁት አልከኝ አገዳደሌን
አደባባይ ላይ በጥይት መደብደቤን።

ረሳችሁኝ ወይ እኔን ነቢዩን ነብስ ሳላዉቅ ጥይት የማዉቅ ምግብ ሳልጠግብ
ባሩድ የቃምኩ።
በሉ አሺ እኔንስ ተዉኝ አንድ ፍሬ ልጅ ነዉ አያዉቅም ብላችሁ እርሱኝ

ግን . . . . ግን ረሳችሁት ወይ አሰፋ ማሩን
ወገኔን ባለ ስጋዉ ማረሩን።

ተረሳችሁ ወይ የአዋሳ አበሳ . . .
ሲዳማ “ሲዳማ” ልሁን ባለ እራሱን በጥይት ሲበሳ።

ለመዳችሁ ወይ የአኝዋክን እልቂት፤
መሬቴን ባለ ጋምቤላ ሲገፋ
ጎጀዉ ተቃጥሎ እሱ ሲደፋ።

አረ አንዴት . . . . እኮ እንዴት ይረሳል
የሽብሬ ሞት. . . . ወንድሞቼን አትንኩ ባለች
እሷ እንደወጣች የቀረች።
ስንቱን ጠርቼ ልጨርሰዉ ማንን ጠቅሼ ማንን ልተዉ።
ምስክር ከሆነ ችግራቸሁ
ቃል ብቻ ከሆነ እምነታችሁ .....
ለቃልማ. . . . .ለቃልማ እኔ አልበቃም ወይ
እኔ ነቢዩ የሁሉም ታናሽ ጨቅላዉ ህፃኑ።
በሷ ንገሩኝ ምን ይበጃል ከኔ ሌላ ምስክር፤
እኮ ምን ይባላል እኔዉ ሞቼ ከኔ ጋር ክርክር . . . .
ከተሰዋ ሰዉ ጋር ድርድር ።
ማን አለና ህይወቱን የሰጠ እማኝ ፤
እስኪ ቅረበኝ ወገኔ እባክህ ስማኝ . . . .
ማን ይምጣልህ ከነቢዩ በላይ እማኝ።
እኔ አይደለሁ ወይ የህጻን ሰማእት ተምሳሌት
አልደፈርም ባይ ኢትዮጵያዊነት።
እኮ እንዴት ይረሱ አግአዚን የተጋፈጡት
ባርነትን እምቢኝ ብለው ደረታቸውን ለፋሺስቶች ጥይት የሰጡት።

…………………………………………………………………………………………………………

## የኦሮሞ ተወላጆች የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጠየቁ

በዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ የሚገኘው የኦሮሞ ማኅበረሰብ ድርጅት፣ አቶ በቀለ ገርባ እና አቶ ኦልባና ሊሌሳን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጥያቄ አቀረበ። ጥያቄው የቀረበው የኦሮሞ ወጣቶች ራስ አገዝ ማኅበር፣ የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ሊግና የኦሮሞ ድጋፍ ቡድን የተዘጋጀው ደማቅ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ነው። ሰልፈኞቹ ከአቶ በቀለ ገርባ እና ከአቶ ኦልባና ሌሊሣ በተጨማሪ በስም የተጠቀሱት ወልቤካ ለሚ፣ አደም ቡሣ፣ ሃዋ ዋቆ፣ ሞሐመድ መሉ፣ ደረጀ ከተማ፣ አዲሱ ምክሬ እና ገልገሎ ጉፋ በእሥር ላይ እንደሚገኙ የሠልፉ አስተባባሪዎች ለ ቪ ኦ ኤ ተናግረዋል፡፡

ግፈኛው የወያኔ አገዛዝ አቶ በቀለ ገርባን፣ አቶ ኦልባና ሌሊሣን፣ እንዲሁም ሌሎቹንም ሰባት የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ በፖለቲካ ምክንያት ተይዘው የረዥም ዓመታት እሥራት የተፈረደባቸውን ሰዎች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈታ፤ የኃይለማርያም ደሣለኝ አስተዳደር የኢትዮጵያን ሕገመንግሥት እንዲያከብር፣ ከፍርድ ውጭ የሆኑ ግድያዎችንና ንፁሃን ሰዎችን ያለክስ ለተራዘመ ጊዜ ማሠሩን እንዲያቆም የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ጫና እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ዩናይትድ ስቴትስ ለኢትዮጵያ የምጣኔ ኃብት ድጋፍ ከመስጠቷ በፊት የፖለቲካ እሥረኞች ሁሉ እንዲፈቱ አስገዳጅ ጫና እንድታደርግ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የኦሮሞን ሕዝብና የሌሎቹንም ሰብዓዊ መብቶች፣ ሃሣብን የመግለፅና የመደራጀት ነፃነቶችን እንዲያከብር አሜሪካ እንድትጠይቅ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት መሠረታዊ የሆኑ የዜጎችን መብቶች የሚጥሱ አዳዲስ ሕግጋትን ሁሉ፣ በተለይ ፀረ-ሽብር የሚባለውን ሕጉን፣ የፕሬስ ሕጉን፣ የረድዔት ድርጅቶች በሃገሪቱ ውስጥ እንደልባቸው እንዳይንቀሣቀሱ የሚገድበውን የሲቪል ማኅበራት ማቋቋሚያ ሕጉን፣ እንዲሁም ስካይፕንና ሌሎችም የሚድያ አገልግሎት ዘዴዎችን መጠቀምን ሕገወጥ የሚያደርገውን በቅርብ ያወጣውን ሕጉን እንዲሠርዝ እንዲሁም የሃይማኖት ነፃነትን እንዲያከብር እና በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥም ጣልቃ መግባት እንዲያቆም የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት እንዲጠይቅ የሚሉ ጥያቄዎች መቅረባቸውን ይሄው ቪ ኦ ኤ ዘግቧል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ድርጅቶቹ የላኩለትን መግለጫ በመጥቀስ እንደገለጸው የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ላይ ትርጉም ያለው ጫና ማሳደር ካልቻለ ዘረኛው አገዛዝ በኦሮሞ እና በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት ይቀጥላል ብለዋል። የኦሮሞ ተወላጅ ለስቴት ዲፓርትመንት በቀጥታ ለፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በግልባጭ በላኩት ደብዳቤ ላይ አናሳው የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት (ህወሀት) 40 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ህዝብ በሚወክለው የኦሮሞ ህዝብ ላይ ጥቃት እየፈጸመ ነው ማለታቸውን ኢሳት ዘግቡአል።

## ወያኔ ኢህአዴግ ለምርጫ ተብየው ቅስቀሳ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እየበተነ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ያስቀመጠው የምርጫ ኮታ ባለመሙላቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ላልተመዘገቡ ሰዎች በሚል ሽፋን ምርጫ ቦርድ ለተወሰኑ ተጨማሪ ቀናት ምዝገባውን እንዲቀጥል በውስጥ ደብዳቤ ማዘዙን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

ዘጋቢያችን ይወያኔ ኢሃዴግ የውስጥ አዋቂ ምንጭ አነጋግሮ ባገኘው ምላሽ ከፋፋዩ የወያኔ አገዛዝ በርካታ ኢትዮጵያዊያንን በአንድ ለአምስት የጥርነፋ ስትራቴጂው ሳይወዱ በግድ ያደራጀው፣ በምርጫ ወቅት የምርጫ ካርድ ያወጡ ሰዎችን እንዴት አድርጎ የምርጫ ካርዳቸውን ወደ እራሱ የድምጽ ኮሮጆ የሚያስገባበትን የተጠና ዘዴ ለመተግበር ዝግጅቱን በማጠናቀቁ ነው ማለታቸውን ገልጹአል።

ይህ በንዲህ እዳለ ወያኔ ኢህአዴግ ሊያካሂድ ባሰበው የአካባቢ ምርጫ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይሳተፍ 39ኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥሪ ማቅረባቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቱአል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ፓርቲዎቹ ህዝባዊ ጥሪውን ያቀረቡት "ኢህአዴግ ስለ አካባቢ ምርጫ የሰጠው መግለጫ የጥያቄዎቻችንን ትክክለኛነትና አግላይ አቋሙን ያረጋገጠበት ነው" በሚል ርዕስ ባወጡት መግለጫ ነው። እነኝሁ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መላው የአገራችን ህዝብም የምርጫው አካል በመሆን ኢ-ዲሞክራሲያዊና ኢህገ-መንግስታዊ ለሆነ አካሄድ ይሁኝታ እንዳይሰጥ ጥሪ እናቀርባለን በማለትም ህዝቡ በምርጫው እንዳይሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል። ፓርቲዎቹ በመግለጫቸው ማጠቃለያ በተባበረና በተቀናጀ ህዝባዊና ሰላማዊ ትግል ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት፤እንዲሁም ከድርጅታችን ይልቅ ለአገራዊ የህዝብ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት በትብብር ለመሥራት ቃላችንን እናድሳለን ማለታቸውን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል።

## በደል እንዴት ይራሳል?. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

በሉ እንገዲህ ስሙኝ በደል አትርሱ በደል አትልመዱ . . . . .
ሞቴን በሞታችሁ ዉለዱ፤ የሞትኩለትን አርማ አንሱ መስዋዕትነቴን አትርሱ።
በተለይ . . . . . በተለይ በደል አትርሱ . . .

በሉ እንገዲህ ስሙኝ በደል አትርሱ በደል አትልመዱ . . . . .
ሞቴን በሞታችሁ ዉለዱ፤ የሞትኩለትን አርማ አንሱ መስዋዕትነቴን አትርሱ።
በተለይ . . . . . በተለይ በደል አትርሱ . . .

እንዴት ይረሳል በደል
እንዴት ይለመዳል ሰዉ ሲገደል።
አረ አንዴት ይረሳል በደል ወጣት እንዳዉሬ ታድኖ ሲታሰር
ኮረዳ ተሰብስቦ ሲደፈር።
በሉኮ ንገሩኝ በደል እንዴት ይረሳል አበሻ እንደጎመን ሲቀቀል
ወገን ባደባባይ በጥይት ሲቃጠል ።

እባካችሁ ንገሩኝ በደል እንዴት ይረሳል አግአዚ ገድሎ ሲወደስ
በደል እንዴት ይለመዳል የሰዉ ልጅ ጥርስ በሽቦ ሲነቀስ

ንጹህ ዜጋ በየመንገዱ ሞቶ ሲለቀስ.......
እኮ እንዴት ይረሳል በደል ወጣት እንደ ምጣድ ሲታመስ
ሀይማኖታችን ሲረክስ አንድነታችን ሲፈርስ።

ስሙኝ . . . . . ስሙኝ ... ወገኖቼ እንደ እባብ ቆዳ ጀርባችሁ የሚላጥ
እንደ ላም ወተት ወዛችሁ የሚናጥ፣

ወያኔ . . . . . ወያኔ . . . .እንደ ብርቱኳን ልጦ ግጦ፣
ወዝ ላባችሁንን መጥጦ፣
ሊዉጣችሁ ነዉ አላምጦ
መተካካት እያለ ትብስን በትባስ ለዉጦ።

ይሉናል ከሰማይ ቤት ፡
ቁልቁል እያዩን በትዝብት።

እኔ ተስፋ ግን ጥሪያቸውን ሰምቻለሁ ፡
በልጅነት እድሜዬ የተቀማሁትን ብሩህ ተስፋ
እውን ላደርግ በሞቴ ፍትህን ለማስፈን ቆርጫለሁ፡

ለሰንደቁ ክብር ለኢትዮጵያ አንድነት
ለህዝቧ እኩልነት
ህይወቴን ልገብር ጉዞ ጀምሬአለሁ ፡
ህዝባዊ ሀይሉን ተቀላቅያለሁ።

ወንድሜ ምን እንዳይቀር በቃህ ተነስ፣
እህቴ ምን እንዳይቀር በቃሽ ተነሽ፣
እስር አለ ታሰሩ፡ ሞትም አለ ሙቱ፣
ከሃዲስ ይሞት የለ ክህደት ሞልቶ ባንደበቱ፣

የእዉነት ሞት ግን
ህይወት ነዉ እስኪ ለህይወት ሙቱ
እስኪ ለህይወት ሙቱ!

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org